


# የዩኒቲ ራእይ

## ከህንድ ዩኒቲ የምትባል የአንድ ወጣት ሴት የፍጻሜ ዘመን ራእይ።

## (የሺሎንግ መነቃቃት ክፍል / ፓርት ኦፍ ዘ ሺሎንግ ሪቫይቫል)

የኢየሱስን ራእይ ያየሁበት ቀን በእሁድ የወጣቶች ጊዜ ላይ ነበረ፣ ማርች 9፣ 2006።



ኢየሱስ ስለ ሦስት ነገሮች ነገረኝ፤

1. የቅዱሳን መነጠቅ።
2. የአውሬው አገዛዝ።
3. የእግዚአብሔር ፍርዶች።

የእርሱን (የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን) ፈቃድ ያደረጉ ሁሉም ቅዱሳን በመነጠቅ ውስጥ ተወስደው ነበረ፣ ኢየሱስ በሠማያት መሃል መጥቶ ወደታየበት። እርሱ በመሬት ላይ ያሉ የእርሱን ፈቃድ ያደረጉትን ሁሉንም ወሰደ። በመሬት ውስጥ ተቀብረው የነበሩ ታማኞች ጭምር በመነጠቅ ጊዜ ወደ ሠማይ ውስጥ ተወስደው ነበረ።

ከመነጠቁ በኋላ፣ መላእክት ከአንድ 666 ከሆነ ዘንዶ(ድራጎን) ጋር ሲዋጉ አየሁ። እሱም ተሸነፈ፣ እናም ለእሱ በሰማይ ምንም ስፍራ አልተገኘለትም፣ ስለዚህ እሱ ወደመሬት ወደቀ። ዘንዶውም ለሚቆጠሩ ዓመታት በምድር (በመሬት) ላይ እንደሚገዛ ተናገረ።



እሱም ሄደ እና ከዛ አሥር ቀንዶችና ሰባት ራሶች የነበሩት ሌላ አውሬ መጣ። እሱም የስድብ ስሞች የተጻፉባቸው ዘውዶች ራሱ (ጭንቅላቱ) ላይ አድርጎ ነበረ።

*አስተዋዋቂ: እሱ ሰው ይመስል ነበር?*



እሱ ሰው ይመስል ነበር፣ ግን እጅግ እጅግ አስፈሪ። በእሱ ንግስና ጊዜ፣ እሩዝ እንኳ የእሱ (የአውሬው) ምልክት በላዩ ላይ ታትሞበታል። ብር እንኳ የአውሬው ምልክት በላዩ ላይ ታትሞበታል። በእሱ (በአውሬው) ያመኑ ሰዎች የእሱ ምልክት በላያቸው ላይ ታትሞባቸዋል፣ ምልክቱም 666 ነበረ።



*አስተዋዋቂ: እሱ በሁሉም ንግድ (ግብይት) ላይ የ666ን ማህተም አድርጓል? ስለዚህ በኢየሱስ ያምኑ የነበሩ ላይ ምን ደረሰ (ሆነ)?*

በኢየሱስ ያምኑ የነበሩ እነዛ፣ በዛ ሰዓት (ጊዜ)፣ እጅግ በትልቁ ይሰቃያሉ። በህይወት እያሉ ስጋቸው ይቆረጣል፣ ዓይኖቻቸው በጉልበት ይወጣል። የእነሱ ጉሮሮ ይሰነጠቅና በግዙፍ ኮንቴይነሮች ውስጥ ይጠበሳሉ።

ኢየሱስ በድጋሜ ወደ መሬት (ምድር) ሲመጣ ወደታች መሬት ላይ ይመጣል (ይሆናል) ። ዘንዶው፣ 666 የነበረው፣ የኢየሱስን ክብር ሲያይ፣ ዘንዶው የኢየሱስን ክብር አልቻለውም እና ሸሸ። ኢየሱስ በድጋሜ ሲመጣ፣ ሞተው የነበሩ፣ በመነጠቁ ጊዜ ከጌታ ጋር ወደገነት ሳይሄዱ መሬት (እዚህ ምድር) ላይ ቀርተው የነበሩ ከመቃብራቸው ይነሳሉ።



መላእክቱ መለከታቸውን ይነፋሉ፣ ለእግዚአብሔር የፍርድ ቀን ለመሄድ ሁሉም ሙታን ከመቃብራቸው ይነሳሉ።

*አስተዋዋቂ: ግሩም፣ ግሩም፣ እሺ ሌላ ምን አለ ዩኒቲ?*



ከዛ ኢየሱስ ፍየሎቹን ወደ ግራ እና በጎቹን ወደ ቀኝ አደረጋቸው። እኚህ ፍየሎች የእርሱን (የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን) ፈቃድ ያላደረጉ እና የ666ን ምልክት የነበራቸው ናቸው።

በቀኙ የነበሩት የበግ ጠቦቶች ነበሩ። እነርሱ የመስቀል ምልክት ነበራቸው እና የኢየሱስን ፈቃድ ያደረጉ እነርሱ ናቸው።

ኢየሱስ በቡድን ለይቷቸው የነበሩት ፍየሎቹና በጎቹ ላይ፣ እግዚአብሔር እያንዳንዱ ሰው ላይ ፈረደ። እና እያንዳንዱ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ፍርድ ተሰጠው። እና የእያንዳንዱ ሰው ኃጢአቶች በቲቪ (በቴሌቪዥን) ስክሪን ላይ ታየ።



እግዚአብሔር ጠየቀ፣ "*ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ሰው ሲመሰክርልህ / ሲመሰክርልሽ፣ አምነህ(ሽ) እና ንስሃ ገብተህ(ሽ) ነበር ወይስ አልነበረም?*" እነሱ "አይደለም / አልነበረም" ካሉ ከዛ እነሱ ወደ ሲኦል ተፈረደባቸው። ወደ ሲኦል የተጣሉት፣ ገደብ (መጨረሻ) ወደሌለው ጉድጓድ ውስጥ ሲወድቁ አየሁ። እነሱ ወደ ጉድጓዱ ወደቁና ምንም ቦታ ሳይደርሱ ተወርውረው ወዲያ ወዲህ አሉ። እዛ በጣም የነደደ የጦፈ ሞቃት እሳት ነበረ። ጮኹ እና ኢየሱስን ምሕረት እየለመኑ እጅግ ጮኹ።

በትሎች፣ በትላልቅ እባቦች እና በሲኦል እሳት የተሞላ አየሁኝ። እዛም ጭምር ሰዎች አየሁ። ትሎቹ በአንዱ የአፍንጫ ቀዳዳ ውስጥ ይሄዱና በሌላኛው ውስጥ ይወጣሉ። አንድ ሲባንዋዊ ትልቅ አባ ጨጓሬ የአንድ ሰው ጉንጭ ላይ ተጣብቆ አየሁ። አንድ እባብ በአካሉ ላይ ተጠምጥሞ እና አባ ጨጓሬዎች በሰዎች አካል (ሰውነት) ላይ ሲሳቡ አየሁ።

**ንስሃ በመሬት (በዚህች ምድር) ላይ ብቻ ነው ያለው እና ከሞት በኋላ ባለው ሕይወት አይደለም ንስሃ ያለው**

*አስተዋዋቂ: ከዛ በኋላ ምን ሆነ?*

ኢየሱስ አለ "*እናንተ ንስሃ የምትገቡበት ጊዜ አሁን ነው። በዚህ መነቃቃት እናንተ ትድናላችሁ።*" ኢየሱስ ስለሚወደን (ስለሚያፈቅረን) ይህን መነቃቃት (ሪቫይቫል) ሰጠን።

*አስተዋዋቂ: ሌላ ምን አለ ዩኒቲ?*

ሁሉም ይህ ነው። *[የዚህ ራእይ ፍጻሜ]* ***[ዩኒቲ በአውስትራሊያ ውስጥ ስለሚሆነው መነቃቃት! ሌላ ራእይ/ህልም ነበራት]***



*አስተዋዋቂ: በአውስትራሊያ የት፣ በየትኛው ከተማ?*

*[ዩኒቲ በራእይዋ / ህልሟ ላይ የትኛው ከተማ እንደተወሰደች የምታውቀው አትመስልም]*

በአንድ እሁድ ኢየሱስን አገኘሁት እና እርሱ አንዳንድ አስደናቂ ነገሮችን ገለጠልኝ። ኢየሱስ በተጨማሪ ወደ አውስትራሊያ ወሰደኝ፣ አራት ጓደኞቼንም አገኘሁ፣ ጀን፣ ኬኒ፣ ማርክ እና ሜሪ። ብዙ ሰዎች ደስተኛ መስለው፣እያሸበሸቡ (እየደነሱ) እና እየዘመሩ አየሁ። እነርሱ መነቃቃቱን ቀምሰውታል። እኔ ከእነርሱ ጋር እየዘመርኩና እያሸበሸብኩ (እየደነስኩ) እና ደስተኛ ነበርኩ ምክንያቱም ኢየሱስ በአውስትራሊያ መነቃቃት እንዲኖር አድርጓል። በዛ የአውስትራሊያውያን ቤተ ክርስቲያን ብዙ መላእክትን በቤተ ክርስቲያኑ በውስጥና በውጪ አየሁ። እነርሱ ዙሪያውን በክቦች እየበረሩ ነበረ። እነርሱ መለከቶቻቸውን እየነፉ ነበረ እና ለኢየሱስ ምስጋናዎችን እየዘመሩና እያመሰገኑ ነበረ። እና አንድ ቀን እዚሁ ቦታ እንደሚወስደኝ እና በድጋሜ እንደምንገናኝ ነገረኝ።

*[የቪዲዮው ፍጻሜ]*

***http://www.youtube.com/watch?v=Fz5In54DLpY***

ጌታ እና አዳኝ አምላክ ፈጣሪ የሹአ ሃማሺያክ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ አለ: -

[*ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ፤ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፋ የሚቻለውን ፍሩ።* የማቴዎስ ወንጌል 10:28

ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታል፤ ስለ እኔ ግን ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ያገኛታል። የማቴዎስ ወንጌል 16:25

ኢየሱስም። ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል፤

ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም፤ ይህን ታምኚያለሽን? አላት። የዮሐንስ ወንጌል 11:25-26

ኢየሱስም። እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም። የዮሐንስ ወንጌል 14:6

ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ። እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፤

እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለ ሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው፤ ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር በውሥጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ። John 14:15-17

ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው፤ የሚወደኝንም አባቴ ይወደዋል እኔም እወደዋለሁ ራሴንም እገልጥለታለሁ። John 14:21

በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።

ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ፥ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና። በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል። (John 3:16-18)

[ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአባት ብቻ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን የሚያውቅ የለም።
የኖኅ ዘመን እንደ ነበረ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናልና።
በዚያች ወራት ከጥፋት ውኃ በፊት፥ ኖኅ ወደ መርከብ እስከገባበት ቀን ድረስ፥ ሲበሉና ሲጠጡ ሲያገቡና ሲጋቡም እንደ ነበሩ፥
የጥፋት ውኃም መጥቶ ሁሉን እስከ ወሰደ ድረስ እንዳላወቁ፥ የሰው ልጅ መምጣት ደግሞ እንዲሁ ይሆናል።
በዚያን ጊዜ ሁለት ሰዎች በእርሻ ይሆናሉ፤ አንዱ ይወሰዳል አንዱም ይቀራል፤
ሁለት ሴቶች በወፍጮ ይፈጫሉ፤ አንዲቱ ትወሰዳለች አንዲቱም ትቀራለች።
ጌታችሁ በምን ሰዓት እንዲመጣ አታውቁምና እንግዲህ ንቁ።
ያን ግን እወቁ፤ ባለቤት ከሌሊቱ በየትኛው ክፍል ሌባ እንዲመጣ ቢያውቅ ኖሮ፥ በነቃ ቤቱም ሊቈፈር ባልተወም ነበር።
ስለዚህ እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ፥ የሰው ልጅ በማታስቡበት ሰዓት ይመጣልና።
እንኪያስ ምግባቸውን በጊዜው ይሰጣቸው ዘንድ ጌታው በቤተ ሰዎች ላይ የሾመው ታማኝና ልባም ባሪያ ማን ነው?
ጌታው መጥቶ እንዲህ ሲያደርግ የሚያገኘው ያ ባሪያ ብፁዕ ነው፤
እውነት እላችኋለሁ፥ ባለው ሁሉ ላይ ይሾመዋል።
ያ ክፉ ባሪያ ግን። ጌታዬ እስኪመጣ ይዘገያል ብሎ በልቡ ቢያስብ፥
ባልንጀሮቹን ባሮች ሊመታ ቢጀምር ከሰካሮችም ጋር ቢበላና ቢጠጣ፥
የዚያ ባሪያ ጌታ ባልጠበቃት ቀን ባላወቃትም ሰዓት ይመጣል፥
ከሁለትም ይሰነጥቀዋል፥ እድሉንም ከግብዞች ጋር ያደርግበታል፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል። (የማቴዎስ ወንጌል 24:36-51)]

[ኢየሱስ እንደ ሞተና እንደ ተነሣ ካመንን፥ እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉቱን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና።
በጌታ ቃል የምንላችሁ ይህ ነውና፤ እኛ ሕያዋን ሆነን ጌታ እስኪመጣ ድረስ የምንቀር ያንቀላፉቱን አንቀድምም፤
ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፥ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፤
ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፥ ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን። (1Thessalonians 4:14-17)]
[ከሰው ሁሉ ጋር ሰላምን ተከታተሉ ትቀደሱም ዘንድ ፈልጉ፥ ያለ እርሱ ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና።
የእግዚአብሔር ጸጋ ለማንም እንዳይጎድለው፥ ብዙዎቹም የሚረክሱበት አንድ መራራ ሥር ወደ ላይ በቅሎ እንዳያስጨንቅ፥ ሴሰኛም የሚሆን እንዳይገኝ፥
ወይም ስለ አንድ መብል በኵርነቱን እንደ ሸጠ እንደ ዔሳው ለዚህ ዓለም የሚመች ሰው እንዳይሆን ተጠንቀቁ። Hebrews 12:14-16]
በዚያን ጊዜ ከዓለም መጀመሪያ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያልሆነ እንግዲህም ከቶ የማይሆን ታላቅ መከራ ይሆናልና። የማቴዎስ ወንጌል 24:21
በሁሉም ዘንድ ስለ ስሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ፤ እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል። Mark 13:13።]

[ነገር ግን እላለሁ፥ በመንፈስ ተመላለሱ፥ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ። ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና፥ እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ፤ ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም። በመንፈስ ብትመሩ ግን ከሕግ በታች አይደላችሁም። የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው እርሱም ዝሙት፥ ርኵሰት፥ መዳራት፥ ጣዖትን ማምለክ፥ ምዋርት፥ ጥል፥ ክርክር፥ ቅንዓት፥ ቁጣ፥ አድመኛነት፥ መለያየት፥ መናፍቅነት፥ ምቀኝነት፥ መግደል፥ ስካር፥ ዘፋኝነት፥ ይህንም የሚመስል ነው። አስቀድሜም እንዳልሁ፥ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።

የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው። እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም። የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ። በመንፈስ ብንኖር በመንፈስ ደግሞ እንመላለስ። እርስ በርሳችን እየተነሣሣንና እየተቀናናን በከንቱ አንመካ። 1 ተሰሎንቄ 5:16-26]

[ዳሩ ግን የሚፈሩና የማያምኑ የርኵሳንም የነፍሰ ገዳዮችም የሴሰኛዎችም የአስማተኛዎችም ጣዖትንም የሚያመልኩ የሐሰተኛዎችም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው፤ ይኸውም ሁለተኛው ሞት ነው። Revelation 21:8]

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም አለ:- እኔና አብ አንድ ነን። John 10:30

[ከእርሱ ጋር ኅብረት አለን ብንል በጨለማም ብንመላለስ እንዋሻለን እውነትንም አናደርግም፤ ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ኅብረት አለን፥ የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል። ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፥ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም። በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው። ኃጢአትን አላደረግንም ብንል ሐሰተኛ እናደርገዋለን ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም። 1ኛ የዮሐንስ መልእክት 1:6-10። የዮሐንስ ራእይ 13-22]

በእስራኤል አምላክ በሠራዊት ጌታ፣ በነገሥታት ንጉሥና በጌቶች ጌታ በናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ እርዳታ ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ የተረጎመው፣ ቶማስ ጌታቸው። Translated to Amharic by Thomas Getachew Tuta, hithomasgetachew@gmai1.com